# ማደስ፣ ማጠናከር፣ መልሶ ማደራጀት
# የቀጠና አራት ገጽታ

**ማደስ፤ ፈጠራዊ መርሀ ግብሮች**
ከፍተኛ ጥራት ላላቸው ለተለያዩ በርካታ መርሀ ግብሮች፣ የሚከተሉትን የታቀዱ በቀጠና አምስት የሚገኙትን ጨምሮ ዲሲፒኤስ በከተማይቱ በሚገኙ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ሁሉ ልዩ ፕሮግራሞችን እየነ ደፈ፣ እየዳበረና እያስፋፋ እንዲሁም እያጠናከረ ነው። ይህ አጠቃላይ ገጽታ፣ ልናጠናክርና ልንደግፋቸው የምናቅደውን በቀጠና አምስት በሚገኙ ትምህርት ቤቶች እስከ አሁን በመሰጠት ላይ ያሉትን ፕሮግራሞች አያንጸባርቅም።

### BURROUGHS-TAFT ቅድመ K-8

BURROUGHS-TAFT በአሁኑ ወቅት ወደ Taft ሕንጻ ውስጥ እንዲዛወር የሚደረገው ሥነ ጥበብ ትምህርት ላይ የሚያተኩር ይሆናል። የ Taft መርሀ ግብር ከ Fillmore የሥነ ጥበብ ማዕከልና ከክልሉ የሥነ ጥበብ ለምሳሌም ያህል እንደ Smithsonian እና Kennedy ማዕከላት ጋር በማበር የ Taft መርሀ ግብር፣ በጣም የበለፀጉ የተዋኻዱ የጥበብ፣ በዐይን የሚታይ ኪነጠባትን፣ የፈጠራ ድርሰቶችን ወይም ጽሑፎችን፣ እጅግ ከተጠናከር አጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርት ጋር አንድ ላይ ይሰጣል። በጥበብ የሚደረግ ተሰትፎ፣ የተላያዩ ልጆች ያላቸውን የተላያዩ ዐይነት ዕውቀት ለማጎልበት፣ ብቁ የሆነ ትወዳዳሪንትን እንዲጭብጡ ለማድረግ ተጨማሪ የዕውቀት ዘርፎችን ሊያስገኙ የሚያስችሉ ጎዳናዎችን ለመክፈት ያስችላል።

### EMERY ቅድመ K-8

EMERY **የሣይንስ፣ የቲክኖሎጂ፣ የምህንድስና፣ የሂሳብ (STEM)** ፕሮግራሞችን የሚያካሂድ ት/ቤት በመሆን ከቅድመ K-8 ክፍል ላሉ ተማሪዎች ትምህርት ይሰጣል። የ STEM መርሀ ግብሮች ጠንካር የአጠቃላይ የትምህርት ሥርዓተ ትምህርትን ከሣይንስና ከሂሳብ ጋር በማዋኻድ ትምህርት ይሰጣል። ተማሪዎቹ የምርምርንና ውጤት የማምጣት ችሎታን እንዲያዳብሩ፣ በእውኑ ዓለም ጠንካራ ችግሮች ላይ የተመሠረቱ የግልና የቡድን ፕሮጀክቶች ውስጥ ተሳትፈው በማለፍ የቴክኖሎጂ ክህሎቶቻቸውን ለፕሮጀክት ጥናትና የጥናት ውጤት አቀራርብ የሚረዳ ዕውቀት ይገበያሉ።. የ Emery ፕሮግራምን ሙሉ ቅድመ K-12 STEM ቀጣይ ፕሮግራም በመፍጠር፣ ከተዋጣለት McKinley ፕሮግራም ጋር የማዋኻድ ሰፊ እድል አለ።

### BROOKLAND-BUNKER HILL ቅድመ K-8

BUNKER HILL የ **'REGGIO EMILIA'** የሊጋ የልጅነት ፕሮግራምን ይሰጣል። ይህ ከስድስት ዓመት በታች ላሉ ሕጻናት አያያዝና የትምህርት መርሀ ግብር ታስቦ የተነደፈው የ 'Reggio Emilia' አቀራረብ ሕጻናቱ ብቁ ተወዳዳሪ፣ ጥሩ ሀሳብ አመንጪ፣ ባለ ምናብ፣ አሰተዋይ ተመራማሪና ፈጣሪ ተደርገው እንዲታዩ ይጠይቃል። የ Reggio አቀራረብ ሕጻኑ ከወላጆች፣ ከትምህርት ቤት ሠራተኞችና ከአቻዎቹ ጋር በመገናኘትና በመነጋገር በፈጠራዊ ትምህርት በሚቀሰም ላይ ያተኩራል። የ Peabody አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የ Reggio አቀራረብ ውጤታማነት ያሳየ ሲሆን ዲሲፒኤስም ይህንን ሞዴል በሌሎች ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፋ ይፈልጋል።

### WEBB–WHEATLEY ቅድመ K-8

Webb-Wheatley የ **Montessori** መርሀ ግብርን ያካሂዳሉ። Montessori ትምህርት፣በማዳምጥ፣ በመመልከት፣ ወይም በማንበብ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ሕዋሳቶች አማካይነት በሚካሄድብት ሁኔታ ላይያተኩራል። ልጆች በ Montessori ክፍሎች፣ ከበርካታ ሁኔታዎች መካከል በሚመርጡት መንገድ አማካይንት በራሳቸው ፍጥንት ይማራሉ። በ Montessori ክፍሎች ሕጻናቱ በየሦስት ዓመታት ልዩነትና የዕድሜ ክልል የመደቡ ቡድኖች (3-6፣ 6-9፣ 9-12፣ እያለ) ታላላቆቹ ታናናሾቹን የሚያሰተምሩባቸው የየራሳቸውን ማኅበረሰቦች ይፈጥራሉ። መምህራን ሠልጥነው ስፔሻላይዝድ የምስክር ወረቀት በመያዝ ተማሪዎቹን ከዕድሜ፣ ከችሎታና ከዝንባሌያቸው አንፃር እየለዩና ዝግጁነታቸውን እያረጋገጡ ዕድገታቸውን ይከታተላሉ።

**ማደስ፤ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሚያስፈልገው ሠራተኞችንና ሪሶርሶችን ማሟላት**
ራእያችን፣ ትምህርት ቤቶችን ሁሉ፣ ጥበብን፣ ሙዚቃን፣ እና የስውነት ማጎልመሻንና እንዲሁም ተማሪዎችንና ቤተሰቦችን በማኅበራዊ ስሚታዊ ፍላጎቶች አኳያ የሚረዱ በተግባር ላይ ያሉ ባለሙያች፣ ርእሠ መምህራን በትምህርት ሥራ ላይ እንዲያታኩሩና ለተማሪዎች ተጨማሪ አካዳሚክ ድግፍ መስጠት እንዲችሉ የአስተዳደር ድጋፍ ማበርከት ነው።

አጠቃላይ ሁሉን አቀፍ ለሆነው ለዚህ የሰው ኃይል አደረጃጀት ሞዴል፣ ለ 2008 በትምህርት ቤቶች መዘጋትና መዋኸድ የተነሣ ተማሪዎችን የሚቀበሉ ትምህርት ቤቶችን ቅደም ተከተል እናዋጣለን። ይህም ቅደም ተከተል **Brookland-BUNKER HILL, BROWNE-YOUNG, BURROUGHS-TAFT, EMERY, LANGDON** እንደ **NOYES** ትምህርት ቤቶችን ያሉ ያካትታል።